| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "ዐርበኝነት ፣ ትላንትና ፡ ዛሬ ። " |
| ደራሲ ፤ | ምንደሲል ፡ ፀሓዩ |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፣ ቍ.2013-005 ። |
| ማስታወሻ ፤ | የድል ፡ በዓል ፡ 80 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | (የግል ፡ አስተያየት ። ) |

# ድርሰት

Essay | Essai | مَقال

# ዐርበኝነት ፣ ትላንትና ፡ ዛሬ ።

ምንደሲል ፡ ፀሓዩ ፣

ሚያዚያ ፡ 23 ፡ ቀን ፣ 2013 ፡ ዓ. ፡ ም. ።

———

የዛሬ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፣ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ቅኝ ፡ ግዛቷ ፡ ለማድረግ ፡ የዠመረችውን ፡ ወረራ ፡ ለመመከት ፣ መላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ባስተባበረ ፡ ጦር ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘምተው ፣ ዐድዋ ፡ ለይ ፡ ዐመድ ፡ አደረጉት ። ዐምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ኢጣሊያ ፡ በወረረችው ፡ ባሕር ፡ ምድር ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ የከብት ፡ በሽታ ፡ ገብቶ ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለዕርሻ ፡ የሚኾን ፡ ከብት ፡ ጥፍቶ ፡ ላምስት ፡ ዓመት ፡ አገሪቱ ፡ በረኃብ ፡ መዳከሟ ፡ ኢጣሊያን ፡ አለመጠን ፡ የልብ ፡ ልብ ፡ ሰጥቷት ፡ ነበር ። ያፄ ፡ ምኒልክ ፡ ድል ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ አሰደናቂ ፡ መኾኑን ፡ ለመረዳት ፡ ይህን ፡ ብዙ ፡ ያልተወሳውን ፡ ያረመኔ ፡ ድርጊት ፡ መገንዘብ ፡ ይበጃል ።

ይህ ፡ የዐድዋ ፡ ድል ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ዐርነታቸውን ፡ ያጡ ፡ ሕዝቦች ፡ የነጻነት ፡ ተስፋ ፣ የክተት ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፣ ለኢትዮጵያውያን ፡ ደግሞ ፡ ለመቶ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ያላባራ ፡ የቂም ፡ በቀል ፡ ጥቃት ፡ መነሻ ፡ ኾነ ።

ከዐድዋ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ በ 1922 ፡ ዓ.ም. ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተብለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኾኑ ። ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ በሴት ፡ መውረዳቸው ፡ ለዙፋኑ ፡ ተገቢ ፡ አለመኾናቸውን ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፣ የዘመኑ ፡ ታላላቅ ፡ አስተዳዳሪዎች ፣ በግልጽ ፡ ሲናገሩ ፡ ስለቈዩ ፣ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሥጋት ፡ ምንጭ ፡ ኾኑ ። ምንም ፡ ተቀናቃኝ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በመሉ ፡ ልብ ፡ ለመግዛት ፡ አልተመቻቸውም ። ለኢትዮጵያ ፡ ጠላቶች ፡ ግን ፡ የተመኙት ፡ ደረሰ ። በመኳንንቱ ፡ ያልተማመነ ፡ ንጉሥ ፡ አውሮጳውያንን ፡ የሚቋቋም ፡ ጦር ፡ ለመመሥረት ፡ እንደሚሳነው ፡ ገባቸው ። ብዙ ፡ አልተሳሳቱም ።

ለገዛ ፡ ህልውናቸው ፡ የሚሡጉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፣ መኳንንቱ ፡ ርሰ ፡ ብርሳቸው ፡ እንዳይተማመኑ ፡ ማድረግ ፡ ግድ ፡ ኾነባቸው ። በዚህ ፡ መንገድ ፣ ተስማምቶ ፡ መንግሥት ፡ የመለወጥን ፡ ዐቅም ፡ ነሡት ። የዚህ ፡ ስልት ፡ አንዱ ፡ ውጤት ፣ በዐድዋ ፡ ላይ ፡ የታየውን ፡ ያንድነት ፡ መንፈስ ፡ ክፉኛ ፡ ማድከም ፡ ኾነ ።

ዳግመኛ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ አሰፍስፋ ፡ የምትጠብቀዋ ፣ የፋሺዝም ፡ ስካር ፡ የዐድዋን ፡ መሪር ፡ ቅጣት ፡ ያስረሳት ፡ ኢጣሊያ ፡— "ጊዜው ፡ አኹን ፡ ነው" ፡ ብላ ፡ ባፍሪቃ ፡ የብስ ፡ በመጠንም ፡ በዘመናዊነትም ፡ ዘምቶ ፡ የማያውቅ ፡ ኀይል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ አዘመተች ።

ከጠበቀችው ፡ በላይ ፡ የተዋጋት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ የሚወርድበትን ፡ የመድፍና ፡ የቦምብ ፡ ዶፍ ፡ ችሎ ፡ ባለው ፣ ዐድዋ ፡ በዘመተ ፡ መሣሪያው ፡ ግሥጋሤዋን ፡ አቆመው ። ኢጣሊያ ፡ ግን ፣ ድንጋጤዋ ፡ ባረመኔነት ፡ ተለውጦ ፡ በዓለም ፡ በተወገዘና ፡ በጦርነት ፡ ሕግ ፡ በተከለከለ ፡ መርዝ ፡ ዘማቹን ፡ ፈጀችው ። ማይጨው ፡ የነበሩት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ የጦርነቱን ፡ አዝማሚያ ፡ አይተው ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ አፈገፈጉ ። ከዚያም ፡ በጅቡቲ ፡ አድርገው ፡ ካገራቸው ፡ ወጡ ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የለቀቁለትን ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ዐዲስ ፡ አበባን ፡ የጣሊያን ፡ ጦር ፡ አለብዙ ፡ ችግር ፡ ለመያዝ ፡ ተመቸው ። መላው ፡ አገር ፡ ግን ፡ ከማይጨው ፡ መልስ ፡ ዐርበኝነት ፡ በወጣው ፡ አገር ፡ ወዳድ ፡ ሕዝብ ፡ ብርታት ፡ ላምሰት ፡ ዓመት ፡


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፣ 2013 ፡ ዓ.ም. ።

ለጣሊያንና ፡ ለባንዳ ፡ ሲኦልን ፡ ኾነበት ።

የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ማይጨው ፡ ላይ ፡ መሪ ፡ ሲያጣ ፡ ተሰፋ ፡ ቈርጦ ፡ አልተበተነም ። በያለበት ፡ ነፍጡን ፡ ይዞ ፡ በታላላቅ ፡ አዝማቾች ፡ እየተመራ ፡ ጦርነቱን ፡ ቀጠለ ። ማይጨው ፡ ያልዘመተውም ፡ ዕልቆ ፡ መሳፍርት ፡ የሌለው ፡ አገር ፡ ወዳድ ፡ ቤቱን ፡ ትቶ ፡ (ከፊሉም ፡ ቤቱን ፡ አቃጥሎ) ፡ ለባዕድ ፡ አልገዛም ፡ ብሎ ፡ ዐርበኝነት ፡ ወጣ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በታሪኩ ፡ መሸነፍን ፡ ያላወቀ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፥ ፈሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ አሸነፈችኝ ፡ ብሎ ፡ እንኳን ፡ ለመማረክ ፡ ለማመን ፡ እንኳ ፡ ትንሽ ፡ ዝንባሌም ፡ አላሳየም ። የኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፥ እንደለመደው ፡ መሸነፉ ፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ በፈጣሪው ፡ ተማምኖ ፡ የጦር ፡ ሥርዐትን ፡ ሳያጓድል ፥ ለጠላት ፡ አረመኔነት ፡ ባረመኔነት ፡ ሳይመልስ ፡ ያርበኛ ፡ ክብሩን ፡ ጠብቆ ፡ ተዋጋው ።

ኢጣሊያም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ አሰተዳደሯን ፡ ለመዘርጋት ፡ ስታስብ ፡ ዋና ፡ ያለችው ፡ ሥራ ፥ ያገሪቱን ፡ ሕዝብ ፡ በዘር ፡ ለያይቶ ፡ የሚከልል ፡ "ካርታ" ፡ [ቢጋር] ፡ መንደፍ ፡ ነበር ። እንደሚታወቀው ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፥ ቀደም ፡ ብላ ፡ ለወረራው ፡ ስትሰናዳ ፥ ኢትዮጵያ ፡ በጨቋኝና ፡ በተጨቋኝ ፡ የተከፈለ ፡ ሕዝብ ፥ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ አዋርዶና ፡ አስገብሮ ፡ የሚኖርባት ፡ ፍተሕ ፡ አልባ ፡ አገር ፡ እያሠኘች ፡ በብዙ ፡ ያውሮጳ ፡ ደራስያን ፡ መርዟን ፡ ስታሠራጭ ፡ ቈይታለች ። ይህም ፥ ዐድዋ ፡ የመለሳት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስለ ፡ ገባት ፡ ነበር ። እንኳን ፡ ዕቅዷን ፡ እዳር ፡ ልታደርሰው ፥ ያገሪቷን ፡ ዐሥር ፡ በመቶ ፡ እንኳ ፡ መቈጣጠር ፡ አልቻለችም ።

ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ዐርበኛው ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ሰሜን ፡ ደቡብ ፥ ምሥራቅ ፡ ምዕራብ ፡ ሳይል ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ መድረሻ ፡ አሳጣው ። ወደ ፡ መጨረሻውም ፥ ወራሪው ፡ ጦር ፡ በየታላላቁ ፡ ከተሞች ፡ ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ መሽጎ ፡ መውጫ ፡ ዐጣ ።

ካምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ያመነችዋ ፡ እንግሊዝ ፡ ተራዋን ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ስትቀሠፍ ፥ በጀርመን ፡ ከዚያም ፡ በፋሽስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ጦርነትን ፡ ስላወጀች ፥ አገሯ ፡ የተሰደዱትን ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ ዐጅባ ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለማዝለቅ ፡ ወሰነች ። እሱዳን ፡ በነበሩና ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በእንግሊዝ ፡ መኰንኖች ፡ በሠለጠኑ ፡ አገር ፡ ወዳድ ፡ ስደተኞችና ፡ በእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ ታጅበው ፥ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ዕድሜ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፥ በድል ፡ አድራጊነት ፡ አገራቸው ፡ ገቡ ።

ኢጣሊያን ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ለመተካት ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ማለቱ ፡ የገባው ፥ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ (ከባሕር ፡ ምድር ፡ በቀር) ፡ የተቈጣጠረው ፡ ዐርበኛ ፡ የንግሊዝን ፡ ጦር ፡ ሥርዐት ፡ አስያዘው ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፥ መመለሳችው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ እንጂ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተዋግቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ካቈየላቸው ፡ ዐርበኛ ፡ እኩል ፡ ድሉ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ተሳናቸው ። በሙሉ ፡ ልብ ፡ ሊያምኑት ፡ አልቻሉም ። ይህም ፡ ሊታመን ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ገብቶ ፡ እንዳገሩ ፡ ልማድ ፡ ደጅ ፡ ሲጠና ፡ የቈየ ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዐርበኛ ፥ መልስ ፡ ሳያገኝ ፡ ያለውን ፡ ጨርሶ ፡ እንደ ፡ እግር ፡ እንደ ፡ እጁ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ዐብሮት ፡ የተንከራተተውን ፡ ጠመንጃ ፡ ሼጦ ፡ ወደያገሩ ፡ አርሶ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሰ ።

ኢትዮጵያ ፡ ከወረራ ፡ ተገላገልኩ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ልማት ፡ ስትሸጋገር ፡ የተደገሰላትን ፡ አላወቀችም ። እምቢ ፡ ባይነቷ ፡ አኹንም ፡ ለጥቃት ፡ ዳረጋት ። ድል ፡ አድራጊነቷ ፡ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ ለነበሩ ፡ የመላ ፡ አፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ ልብ ፡ ሰጣቸው ። ከቅኝ ፡ ገዦቻቸውም ፡ ሲገላገሉ ፡ አረንጓዴ ፣ ብጫና ፡ ቀይ ፡ ቀለማትን ፡ ለሰንደቅ ፡ ዐላማቸው ፡ መርጠው ፡ የኢትዮጵያን ፡ አርኣያነት ፡ አረጋገጡ ። ይህ ፥ ላውሮጳውያን ፡ የማይዋጥ ፡ ድርጊት ፥ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ከዐድዋ ፡ ድል ፡ ዠምሮ ፡ የተከፈተውን ፡ ዘመቻ ፡ አጠነከረው ።

የኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ የከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ተቋማት ፡ እንደ ፡ ተመሠረቱ ፥ በተለይ ፡ በታሪክ ፡ በቀለም ፡ በማኅበረዊና ፡ ባስተዳደር ፡ ጥናቶች ፡ የተሰማሩት ፡ ያውሮጳና ፡ የሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ መምህራን ፡ የወጣቱን ፡ መንፈስ ፡ ከገዥነት ፡ ወደተገዥነት ፡ ለመለወጥ ፡ የጨቋኝና ፡ የተጨቋኝን ፡ ተርክት ፡ ካኑት ። አገሩን ፡ እንዲጠላ ፥ ያባቶቹ ፡ ትውፊት ፡ ከኋላቀርነት ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።

እንደማይገኝበት ፡ አሳመኑት ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የታነጸውም ፡ ትውልድ ፡ በራሱ ፡ የማይተማመን ፥ አውሮጳውያን ፡ ያስተማሩትን ፡ ሰከን ፡ ብሎ ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ዐይን ፡ ማየት ፡ የተሳነው ፥ ዐጭሩን ፥ ሳይገነዘበው ፥ የእነሱ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ኾነ ።

የደርግ ፣ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፣ የኦሮሙማ ፡ ዐምባ-ገነናዊ ፡ ይዘቶች ፡ የተከታተሉት ፡ የዚሁ ፡ ደባ ፡ አስፈጻሚዎች ፡ ኾነው ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያኽል ፥ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ዐዲስ ፡ ብሎ ፡ ያወጣው ፡ ያሰተዳደር ፡ "ካርታ" ፡ [ቢጋር] ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለመከፋፈል ፡ የነደፈችው ፡ "ካርታ" ፡ ግልባጭ ፡ መኾኑ ፡ ታማኝ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚነቱን ፡ ያሳያል ።

ዛሬ ፥ ኦሮሙማ ፥ እንደ ፡ ባዕድ ፥ ሕዝቡን ፡ ጨፍጭፌ ፡ አባርሬ ፡ አዛገሮቼ ፡ አገርኽ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባስተማሩኝ ፡ መሠረት ፡ የሚገባኝን ፡ መሬት ፡ ወስጄ ፡ የቀረውን ፡ ለቀረው ፡ ሕዝብ ፡ ስተው ፥ ጭቊንነቴ ፡ ያበቃል ፡ ብሎ ፡ ተነሥቷል ። ለማመን ፡ የከበደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ጊዜ ፡ ቢፈጅበትም ፥ ቀስ ፡ እያለ ፡ ነገሩን ፡ ከነመነሻው ፡ ተረዳው ። ለዚህ ፡ መቅሠፍትም ፡ መድኀኒቱ ፡ ዳግም ፡ ዐርበኝነት ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝቦ ፤ « አንዴ ፡ ለመቼም ! » ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።